UNITED ARAB EMIRATES
MINISTRY OF ENERGY & INFRASTRUCTURE

Save to Sustain
National Conservation Campaign

# ለቤት ውስጥ ሰራተኞች ዘላቂ
# መመሪያ



# መግቢያ

የ Ministry of Energy and Infrastructure ከሚመለከታቸው የፌደራል እና የአካባቢ ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የ National Energy and Water Demand Side Management ፕሮግራም/መርሃ ግብርን ይቆጣጠራል። ይህም የሀይል እና የውሃ ፍላጎት አስተዳደር መርሃ ግብሮችን፣ የግንዛቤ ጥበቃን እና ቴክኒካል ኮሚቴን ጭምር በሚከታተል ብሔራዊ ቡድን አማካይነት ይከናወናል። ኮሚቴው የቤት ሰራተኞችን ጨምሮ የሃይል እና የውሃ ፍጆታ ጥበቃን በተመለከተ ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ ማሳደግ እና ባህሪን ለመቀየር ያለመ ነው። ለዚህም ይህ መመሪያ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ እና የቤተሰብ ገቢን ለማሻሻል የሚረዱ የእለት ተእለት ባህሪያትን እና ተግባራትን ለቤት ውስጥ ሥራተኞች እና የቤት ባለቤቶች ለማስተማር በመልማዮች እና በስልጠና ማዕከላት ጥቅም ላይ ለመዋል የተዘጋጀ ነው.



# ዓላማ

የሀይል እና የውሃ ቁጠባ ባህሪያትን በቤተሰብ ልምዶች እና ተግባራት ውስጥ በማስተዋወቅ  የቤት ሰራተኞችን ማሰልጠን የኃይል እና የውሃ ፍጆታን ለመቀነስ አስተዋፅኦ ያደርጋል፣ እንዲሁም የቤተሰብ ገቢን በመጠበቅ ወርሃዊ የፍጆታ ክፍያዎችን ይቀንሳል። ይህም የሀገሪቱን ሃብት ለመንከባከብ እና ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎች ዋነኛ መንስኤ የሆነውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ይቀንሳል። እንዲሁም የ National Demand Side Management ፕሮግራም/መርሃ ግብር ለሀይል እና ውሃ ዓላማዎች፤ እና የNational Conservation Campaigን “ለማቆየት ይቆጥቡ” ፤ ዘላቂ ባህሪያትን የሕይወት መንገድ የማድረግ ዓላማን ይደግፋል።

# ሳይንሳዊ ቃላት

| | |
|---|---|
| ዘላቂነት | ሀብቶችን በሚጠብቅ እና የሰውን ልጅ ደህንነት በጊዜ ሂደት በሚያረጋግጥ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሚዛናዊነት አማካኝነት የመጪው ትውልድ የየራሳቸውን ፍላጎት የማሟላት አቅም ሳይቀንስ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎቶች የማሟላት ችሎታ። |
| ታዳሽ ኃይል | እንደ ፀሀይ፣ ንፋስ፣ ውሃ እና ባዮማስ ካሉ ዘላቂ የሆኑ የተፈጥሮ ምንጮች የተገኘ ሃይል ያለማቋረጥ የሚሞላ እና ጥቅም ላይ ሲውል የማያልቅ ነው። ከቅሪተ አካላት ነዳጅ ጋር ሲነፃፀር በአካባቢ ላይ በሚያሳድረው ተጽዕኖዎች እና በካርቦን ልቀት ዝቅተኛነት ይታወቃል። |
| ንጹህ ሀይል | በካይዎች፣ ጎጂ የካርቦን ልቀቶች፣ እንደ የፀሐይ ኃይል፣ የንፋስ ኃይል እና የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ያሉ ምንጮችን ጨምሮ ሳይለቀቁ የሚመረተው ኃይል። ዘላቂነትን ለማግኘት እና አሉታዊ የአካባቢ ተፅእኖዎችን ለመቀነስ  ጥቅም ላይ ይውላል. |
| የፀሐይ ፓነል | በ photovoltaic effect ላይ በመመስረት የ photovoltic ሴሎችን በመጠቀም የፀሐይ ብርሃንን በቀጥታ ወደ ኤሌክትሪክ የሚቀይሩ መሳሪያዎች ናቸው። ኤሌክትሪክን በንጽህና እና በዘላቂነት ለማመንጨት እንደ ታዳሽ የኃይል ምንጭነት ያገለግላሉ። |
| የውሃ መርጨዎች | በመስኖ ውስጥ የውሃ ፍጆታን ለመቀነስ የሚረዳ በእጅ የሚሰራ ወይም ራስ ሰር የመስኖ ዘዴ። |
| የኢኮ-ማጠቢያ ሁነታ | የኃይል ፍጆታ እንዲቀንስ የሚረዳ፣ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ያለው የማጠቢያ ዘዴ። |
| ማጣሪያ | ወደ አሃዱ የሚገባውን አየር ከቆሻሻዎች እና እንደ አቧራ፣ ቆሻሻ፣ የአበባ ዱቄት እና አለርጂን ያሉ ብክለቶች ለማንጻት የሚሰራ የአየር ማቀዝቀዣ ስርዓት ውስጥ ያለ ቁልፍ አካል። |
| ሙልች | የመስኖ ውሃ ትነትን ለመቀነስ አፈር ላይ የሚነሰነሱ የወደቁ ቅጠሎች ወይም የሌሎች ተፈጥሯዊ ቁሶች ቅርፊት። |

# እውነታዎች

በ United Arab Emirates ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምክንያት የሀገሪቱ የአየር ንብረት በተወሰኑ ባህሪያቱ ተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን ይህም ትክክለኛ አሰራርን እና ባህሪ ካልተከተለ በኤሌክትሪክ እና በውሃ ፍጆታ መጨመር ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችላል።
እነዚህ ባህሪያት የሚከተሉትን ያካትታሉ።

ከፍተኛ ሙቀት

ከፍተኛ የእርጥበት መጠን

አቧራ እና አሸዋ

የውሀ እጥረት

ዝቅተኛ ዝናብ

በ United Arab Emirates ውስጥ የመብራት እና የውሃ ፍላጎት በብዛት የሚታየው ከጠዋቱ 2 ሰአት እስከ ምሽቱ 6 ሰአት ነው።

ማቀዝቀዣ በቤት ውስጥ ከጠቅላላው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ውስጥ 70% የሚሆነውን ሲወስድ፤ መብራት ደግሞ ከጠቅላላው የኤሌክትሪክ ፍጆታ 10-20% ይይዛል።

የ United Arab Emirates የተፈጥሮ ሃብቶችን እጥረት ለማካካስ እንደ የፀሐይ እና የንፋስ ሃይል ንፁህ እና ታዳሽ የሃይል ምንጮችን በበለጠ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ላይ ነው።


የፀሐይ ፓነሎች ካልተጸዱ በአቧራ እና በቆሻሻ መጠራቀም ምክንያት 70% ያህል ውጤታማነታቸውን ያጣሉ።



# ትምህርታዊ መረጃ

# የኤሌክትሪክ አጠቃቀምን ምክንያታዊ ለማድረግ መተግበር ያለባቸው ባህሪያት

## ማቀዝቀዣን እና ማሞቂያን በአግባቡ ማስተዳደር




ማቀዝቀዣ ወይም ማሞቂያን በተያዙ ክፍሎች ውስጥ ብቻ መገደብ እና የሙቀት መጠኑን በ23-24 °C መካከል ማድረግ።



ቅልጥፍናን እና የአየር ፍሰትን ለማሻሻል የአየር ማቀዝቀዣ ክፍሎችን በየጊዜው ያጽዱ።



በሞቃት የበጋ ወራት የአየር ማቀዝቀዣውን ውጤታማነት ለማሻሻል እና ቀዝቃዛ አየር እንዳይወጣ በሮች እና መስኮቶች በደንብ መዘጋታቸውን ማረጋገጥ እና በክረምት ወቅት የአየር ማቀዝቀዣዎችን በማጥፋት ረጋ ያለውን አየር መጠቀም።

## መብራት



በተቻለ መጠን በተፈጥሮ ብርሃን ላይ መመርኮዝ እና ባልተያዙ ክፍሎች ውስጥ መብራቶችን ማጥፋት።




የመብራት ቅልጥፍናን ለማሻሻል የመብራት ዕቃዎችን ከአቧራ ንጹህ አድርጎ ማቆየት።

## የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን መጠቀም



እንደ ቫክዩም ማጽጃ እና የልብስ ማጠቢያ ማሽኖችን የመሳሰሉ ከባድ መሳሪያዎችን ከከፍተኛ ሰአት ውጭ መስራት እና በተለይም በከፍተኛ ሰአት ሁሉንም እቃዎች በአንድ ጊዜ ከማሰራት ይቆጠቡ።




የማያስፈልግ የጭስ ማውጫ መሳሪያን ማጥፋት:-

- ወጥ ቤት ውስጥ ምግብ ከማብሰል በኋላ።
- መታጠቢያ ቤት ውስጥ ገላ ከመታጠብ በኋላ።



ከቦታው ሲወጡ ወይም ባልተያዙ በታዎች ላይ ሁሉንም መብራቶች እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ዕቃዎችን ማጥፋት።




ከተጠቀሙ በኋላ እቃዎችን ከዋናው ማብሪያ / ማጥፊያ ያጥፉ እና በሚተኙበት ጊዜ መሳሪያዎችን ከመሙላት ይቆጠቡ።




የልብስ ማድረቂያ በመጠቀም ሀይልን ከማባከን ይልቅ ልብሶችን ከቤት ውጭ ማድረቅ።



የልብስ ማድረቂያ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ብቃቱን ለማሻሻል እና የኃይል ፍጆታን ለመቀነስ ማድረቂያውን በንጽህና መያዝ።

# ማድቤት




የፍሪጅ በር በደንብ መዘጋቱን ማረጋገጥ፣ በማቀዝቀዣው ውስጥ የበረዶ ክምችትን ማስወገድ እና ከማቀዝቀዣው በስተጀርባ ለአየር ማናፈሻ የሚሆን በቂ ቦታ መተዉ።



ቅልጥፍናን እና የህይወት ዘመኑን ሊቀንስ ስለሚችል ማቀዝቀዣውን ከመጠን በላይ ከመጫን ወይም በዘፈቀደ ከመሙላት ይቆጠቡ። በማቀዝቀዣው በር ላይ ያለውን የጎማ ማሸጊያ ቀለበት ሁኔታ በየጊዜው ያረጋግጡ።



የሚወጣውን ሙቀት በሙሉ ያለምንም ብክነት ለመጠቀም የድስቱን መጠን ከምድጃው ጋር ለማመሳሰል ይሞክሩ።




የማብሰያ ጊዜን ለመቀነስ እና ኃይልን ለመቆጠብ በድስቶች ላይ ጥብቅ ክዳንን ይጠቀሙ።




ትንሽ ጊዜ እና ሃይል ስለሚወስድ ውሃን ከድስት ይልቅ በማንቆርቆሪያ ማፍላት ይሻላል።

## ውሃ ማሞቂያ




በማይጠቀሙበት ጊዜ የውሃ ማሞቂያውን ያጥፉ እና ገላዎን ከመታጠብዎ በፊትም በተገቢው ጊዜ ያብሩት።


## ሶላር ፓነሎች



በቤት ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ማይክሮፋይበር ፎጣዎችን በመጠቀም በየወሩ ከአቧራ እና ከቆሻሻ ማጽዳትዎን ያረጋግጡ።

# የውሃ ጥበቃ

## የውሃ ቧንቧ





አፈፃፀሙን ሳይጎዳ ፍጆታን ለመቀነስ የውሃ ፍሰት መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ።




እቃዎችን በእጅ በሚታጠቡበት ጊዜ የውሃ ቧንቧው ያለማቋረጥ እንዲሰራ አይተዉት።

## የገላ መታጠቢያ ጊዜ



የመታጠቢያ ጊዜን ይቀንሱ፤ ጊዜን ለመለካት ቆጣሪን መጫን ወይም የውሃ ፍጆታን ለመቀነስ ውሃ ቆጣቢ የመታጠቢያ ገንዳዎችን መጠቀም ይችላሉ።

## ዝቅተኛ-ፍሰት የመጸዳጃ ቤት አዝራር፡-




ዝቅተኛ ፍሰት ያለው የመጸዳጃ ቤት አዝራር ከሌለ የውሃ ፍጆታን ለመቀነስ በአሮጌ መጸዳጃ ቤቶች ውስጥ የውሃ ቆጣቢ መሳሪያዎችን መትከል ይቻላል።

## ዝቅተኛ-ፍሰት የመጸዳጃ ቤት አዝራር፡-



የቤቱን ወይም የውጪውን በረንዳ ሲያጸዱ እና ሲያጥቡ የንጽሕና ብሩሽ ውሃ ከያዘ ባልዲ ጋር ውሃ መጠቀም ይመከራል.።

# ማጠቢያ ማሽን



የልብስ ማጠቢያ ማሽኑን ሙሉ አቅሙ ላይ ሲደርስ ብቻ ያስጀምሩ፤ ይህም የልብስ ማጠቢያ ዑደቶችን ለመቀነስ ይረዳል፤ በዚህም የውሃ እና የኃይል ፍጆታን ይቀንሳል እና የመሳሪያውን የአሠራር ውጤታማነት ያሻሽላል።




የውሃ እና የኃይል ፍጆታን ለመቀነስ ከተገኘ የኢኮ-ማጠቢያ ሁነታን መምረጥዎን ያረጋግጡ።




የልብስ ማጠቢያ ዕቃዎችን በሚገዙበት ጊዜ በቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ የሚሟሟ ዓይነት መምረጥዎን ያረጋግጡ።



የሻጋታ እና የሳሙና ቅሪቶችን ለማስወገድ የልብስ ማጠቢያ ማሽኑን በየጊዜው ያጽዱ፤ ይህም የልብስ ማጠቢያ ማሽኑን ቅልጥፍና ለመጠበቅ ይረዳል።

# የእቃ ማጠቢያ



እቃዎችን በእጅ ከማጠብ ይልቅ የእቃ ማጠቢያውን ይጠቀሙ።




የውሃ እና የኃይል ፍጆታን ለመቀነስ ከተገኘ የኢኮ-ማጠቢያ ሁነታን መምረጥዎን ያረጋግጡ።



ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ እና የውሃ ፍጆታን ለመቀነስ የእቃ ማጠቢያ ማሽኑን ሙሉ በሙሉ ከተጫነ ብቻ ይጠቀሙ።



መጀመሪያ ሳህኖቹን መንከር እና መጥረግ ይችላሉ ከዚያም ሳሙናውን አጥቦ ለማስለቀቅ ቧንቧውን ብቻ ይክፈቱ።




## አትክልቶችን እና ፍራፍሬዎችን ማጽዳት

አትክልቶችን እና ፍራፍሬዎችን በአንድ ጎድጓዳ ውሃ ውስጥ ይጠቡ እና የተረፈውን ውሃ ኬሚካል ወይም ሳሙና እንደሌለው እያረጋገጡ ተክሎችን ለማጠጣት ይጠቀሙ። .

## ዘመናዊ የመስኖ ዘዴዎች

በመስኖ ጊዜ የውሃ ብክነትን ለመቀነስ እንደ ጠብታ መስኖ ስርዓቶች ወይም የውሃ መርጫን የመሳሰሉ ዘመናዊ ቴክኒኮችን ይጠቀሙ።



## የመስኖ ተክሎች




በከፍተኛ የፀሐይ ብርሃን ምክንያት የሚፈጠረውን ትነት ለማስወገድ በማለዳ ወይም ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ተክሎችን ያጠጡ።



የአፈርን እርጥበት ለመጠበቅ እና የመስኖ ውሃን ትነት ለመቀነስ በእጽዋት ዙሪያ የወደቁ ቅጠሎችን እና ሙልችን ይጠቀሙ።

# ትነትን ለመቀነስ የመዋኛ ገንዳውን መሸፈን

የውሃ ሙቀትን የሚጠብቁ ሃይል ቆጣቢ ሽፋኖችን ይጠቀሙ፤ ይህም ሃይልን እና ውሃን ለመቆጠብ ይረዳል።



# መኪና ማጠብ

በባልዲ ውሃ እና ስፖንጅ በመጠቀም መኪናውን ማጠብዎን ያረጋግጡ እናም ቱቦ ከመጠቀም ይቆጠቡ።



# የቤት እንስሳት

በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ከማጽዳት ይልቅ የቤት እንስሳትን ከቤት ውጭ ባለው ግቢ ውስጥ ውሃ መጠጣት በሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ማጽዳት ይችላሉ።



# ብልሽቶችን ማመልከት



ቧንቧዎችን፣ ቫልቮች እና የውሃ ቱቦዎችን ለማንኛውም አይነት ቀዳዳ በየጊዜው መፈተሽዎን ያረጋግጡ። ምንም አይነት ፍሳሽ ካስተዋሉ፤ ውሃውን በባልዲ ውስጥ ይሰብስቡ እና ስለ ጉዳዩ ለቤቱ ባለቤት ያሳውቁ።

በግድግዳዎች ላይ የውሃ ፍሳሽ ካዩ፤ ለቤቱ ባለቤት ያሳውቁ።

የአየር ማቀዝቀዣ ማጣሪያዎችን ይቆጣጠሩ እና ሲያስፈልግ የቤቱን ባለቤት  ወይም የጥገና ቡድኑን እንዲያዱት ይጠይቁ።

የግብርናውን አካባቢ ያለ ምንም ፍሳሽ እና ብክነት በመስኖ የማልማት ብቃቱን ለማረጋገጥ የመስኖ ሥርዓቱን አጠባበቅ ይከታተሉ ።
ማንኛውም ብልሽት ከተፈጠረ ለቤቱ ባለቤት ያሳውቁ።

የቤቱ ባለቤት በየጥቂት ወሩ ዋናውን የውሃ መዝጊያ ቫልቭ ወቅታዊ ፍተሻ ማድረግ አለበት።

በኋላ ላይ ተክሎችን ለማጠጣት ጥቅም ላይ የሚውል የዝናብ ውሃን በማጠራቀሚያ ውስጥ ይሰብስቡ ።


# ስለወደፊት ትውልዶች ግንዛቤን ማሳደግ

Eco runner

Estidama Craft

DoE EnergiX

# አስፈላጊ አጋጣሚዎች

| አጋጣሚዎች | ቀን | አጭር መግለጫ |
|---|---|---|
| **የምድር ሰዓት** 60 EARTH HOUR | በየዓመቱ በማርች የመጨረሻው ቅዳሜ ይከበራል። | በአለም ላይ ያሉ ግለሰቦች እና ተቋማት በየሀገሩ ከቀኑ 8:30 እስከ ምሽቱ 9:30 ሰአት ድረስ ለአንድ ሰአት አላስፈላጊ መብራቶችን እንዲያጠፉ ተጠይቀዋል። |
| **Peak Hour**   | ጁላይ አንድ | መነሻው፤ ነዋሪዎች አስፈላጊ ያልሆኑ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን በከፍተኛው ሰአት እንዲያጠፉ ይጠይቃል፤ ይህም በ UAE ውስጥ ከጠዋቱ 2:30 እስከ ምሽቱ 3:30 ነው። |

## ምስጋና ለተሳታፊዎች

UNITED ARAB EMIRATES
MINISTRY OF HUMAN RESOURCES
& EMIRATISATION

الإمارات العربية المتحدة
وزارة الموارد البشرية والتوطين

دائرة الطاقة
DEPARTMENT OF ENERGY

هيئة كهرباء ومياه دبي
Dubai Electricity & Water Authority

حكومة الشارقة
هيئة كهرباء ومياه وغاز الشارقة
Government of Sharjah
Electricity, Water & Gas Authority

EtihadWE
الاتحاد للماء والكهرباء

رشّد لتدوم

الحملة الوطنية للترشيد

**Save to Sustain**

National Conservation Campaign

www.ncc.moei.gov.ae

UNITED ARAB EMIRATES
MINISTRY OF ENERGY & INFRASTRUCTURE